# ጾመ ፍልሰታ መሠረቱ ምንድን ነው?
# ለምን እንጾማታለን?
# የምትፈታውስ መቼ ነው?
# በ16 ወይስ በ21?

እንኳን ፀሐይን ለተጎናጸፈችው፣ ጨረቃን ለተጫማችው፣ በራሷ ላይ 12 የከዋክብት አክሊል ለደፋችው ራዕ. 12፥1-6 ለንግሥተ ሰማይ ወምድር ለወላዲተ አምላክ ለቅድስት ድንግል ጽዮን ማርያም የትንሣኤዋና የእርገቷ በዓል በሰላም አደረሰን!

ወላዲተ አምላክ በዚህ ሱባኤ የፈጸምነውን ጾም ጸሎት ስግደታችንን ወደ ልጇ አሳርጋ ለሀገር፣ ለወገን፣ ለቤተክርስቲያን ትንሣኤን፣ ሰላም ደኅንነትን፣ ጸጋ በረከትን፣ መጠበቅን ታሰጠን! አሜን!!!

ልብ ብላቹህ እንደሆነ ተስፋ እያየን ያለነው በዚህች በጾመ ፍልሰታ ነው፡፡ ወላዲተ አምላክ የዐሥራት ሀገሯ የኢትዮጵያ እና የዐሥራት ልጆቿ የኢትዮጵያውያን ነገር ይገዳታልና ወደ ልጇም አጥብቃ ታሳስብልናለችና እንደምታስታውሱት ያን የቤተክርስቲያን ነቀርሳ የዲያብሎስ ሎሌ አባ ጳውሎስንና ያን የሀገር ነቀርሳ እርጉም መለስን ነቅላ ጥላ ዜና ሞታቸውን ያበሰረችን በዚሁ በፍልሰታ ወቅት ነበረ፡፡ ወያኔ አምና በፍልሰታ ተጠናክሮ የተቀሰቀሰበት ተቃውሞ ዘንድሮም እንደገና የተቀሰቀሰበት በፍልሰታ ነው፡፡ ይሄም ነገር ጉዳያችን በወላዲተ አምላክ መያዙን ያሳያልና እንደጀመረች ትጨርስልንና እኛን አበርትታ አጀግና ሀገራችንን እና ሕዝባችንን ከኢጋንንቱ አሸከላ ከወያኔ አገዛዝ ነጻ ታወጣን ትገላግለን ዘንድ፣ የሀገር የወገን የቤተክርስቲያን ጠላት የሆነውን የኢጋንንት ጭፍራ ወያኔን ትደመስስልን ዘንድ ወላዲተ አምላክ ጽዮን ማርያምን ሙጥኝ ብንላት መልካም ነው ወገኖች፡፡

ይህች ጾመ ፍልሰታና ተያይዞ ያለው ታሪኳ "መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ነው!" ብለን በዘልማድ ከምንጠቅሰው የምሥራቅ አብያተክርስቲያናቱ (The Oriental Churches Bible) የሰማንያ አንዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ እንዲሁም የምዕራብ አብያተክርስቲያናቱ (The Occidental Churches Bible) የስድሳ ስድስቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ የሚገኝ አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ወይም መጻሕፍተ ቅዱሳት ማለት 81 ወይም 66 ወይም 72 ብቻ ናቸው የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ የለም፡፡ ከእነኝህ ሌላም በርካታ መጽሐፍ ቅዱሶች አሉ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በ81 ወይም 66 መጻሕፍት ብቻ አለመወሰኑን ወንጌላዊው ሐዋርያ ዮሐንስ ሲያረጋግጥ ወንጌሉ ላይ 21፥25 "ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል!" በማለት የተናገረ በመሆኑ ሐዋርያዊት፣ ትውፊታዊት፣ መንፈሳዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በተቻላት መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተገለጹ ነገር ግን ጌታ ያደረጋቸውን ነገሮች የሚገልጹ የያዙ መጻሕፍትን እውነተኛነታቸውን በመንፈሳዊና ትውፊታዊ የማረጋገጫ መንገዷ እያረጋገጠች ሰብስባ ይዛ ስትጠቀምባቸው ቆይታለች ወደፊትም ትጠቀምባቸዋለች፡፡
ሐዋርያትም መናፍቃኑ "መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ብቻ ነው!" ከሚሉት ከ66ቱ መጽሐፍ ያልተካተቱ መጻሕፍትን እየጠቀሱ ማስተማራቸው ለዚህ ነው፡፡ ለምሳሌ የሐዋርያው የያዕቆብ ወንድም ሐዋርያው ይሁዳ፡፡

ጌታና ሐዋርያቱ በተናገሩት ትንቢት መሠረት ማቴ. 24፥3-28, ሮሜ. 16፥17, 2ኛ ቆሮ. 11፥13, 1ኛ ጢሞ. 4፥1 ከጊዜ በኋላ የተፈለፈሉት መናፍቃን ግን ይሄው ወንጌላዊ ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ለዚሁ ለራእይ መጽሐፉ ብሎ በ22፥18 ላይ "በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል!" በማለት የተናገረውን ቃል ይጠቅሱና መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ይሄ ብቻ ነው ይላሉ። መቸም የመናፍቅ ነገር አያስተውሉም እንጅ "በዚህ የትንቢት መጽሐፍ ...." ብሎ ምንና የቱን ማለት እንደፈለገ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦላቸው ነበረ። እነሱን የሚመስላቸው መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ጊዜ የተጻፈ መጽሐፍ ነው የሚመስላቸው። ከሊቀ ነቢያት ሙሴ እስከ ጌታ በ1700 ዘመን ውስጥ በጣም በተራራቀ ዘመን የተጻፉ የተለያዩ መጻሕፍት አንድ ላይ የተጠረዙ መሆናቸውን አያውቁም። አሪት ዘፍጥረት ከተጻፈ ከ1700 ዓመት በኋላ ነው ራእየ ዮሐንስ የተጻፈው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተካተቱት መጻሕፍት ራእየ ዮሐንስ መጨረሻ ላይ የተጻፈ መጽሐፍ በመሆኑ መጨረሻ ላይ በመጠረዙ በአጋጣሚ ሆኖ ከላይ ያስቀመጥኩት ቃልም በዚሁ የራእይ መጽሐፍ የመጨረሻ ምእራፍ ላይ መቀመጡ መናፍቃኑ ለማወናበድ ተመቻቸው። ይሁንና እውነታው እንደገለጽኩላቹህ መናፍቃኑ ከሚሉት የራቀ በመሆኑ እነሱ የሚሉት ነገር እጅግ አላዋቂነታቸውን ያሳይ ካልሆነ በስተቀር የሚፈጥርላቸው ፋይዳ አይኖርም።

ከእነኚህ ጌታ ካደረጋቸው ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቃለሉት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ካልተጠቀሱት ካልተገለጹት ነገሮች አንዱ የወላዲተ አምላክን እረፍት አስመልክቶ ሐዋርያቱና ጌታ ያደረጉት ነገር ነው። ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተካተቱት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተካቶ ባይገኝም ይብላኝላቸው ለአዳዲሶቹ ከዘመን በኋላ ለተፈጠሩት የእምነት መሰል ሐሰተኛ ድርጅቶች እንጅ ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን ጌታ እንደመሠረታት ጥንታዊትና ትውፊታዊ ትስስሯ ሳይቋረጥ የመጣች የዘለቀች በመሆኗ ወንጌላዊው ዮሐንስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተካተቱት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ያልተገለጹ ጌታ ያደረጋቸው ተግባራት እንዳሉ እንደተናገረው ሁሉ ቤተክርስቲያን ጥንታዊትና ትውፊታዊት በመሆኗ እነኝህን ተግባራት የሚገልጹ መጻሕፍትን ለማግኘት አልተቸገረችም።

እነኝህ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉ ክፍተቶችን፣ ያልተሟሉ ታሪኮችን የሚሞሉና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚነሡ አወዛጋቢ ጥያቄዎች በቂና አጥጋቢ ምላሽ እንዲገኝላቸው የሚያደረጉት። ያለእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስ ምሉዕ አይደለም። በርካታ የማይሞሉ ክፍተቶችና የማይመልሳቸው ጥያቄዎች አሉበት። በዚህ ምክንያት ክርስትና በምዕራቡ ዓለም መስመር ሊስት ችሏል። በቂና አጥጋቢ ምላሽ መስጠት የማይችል ሆኖ በኑፋቄ ተወርሷል።

ብዙዎቻቹህ በርእስ መልክ ላቀረብኩት የፍልሰታ ጾም መፈቻ ጥያቄ ስትመልሱ "ይሄማ ምን ጥያቄ አለው በነሐሴ 16 ነዋ!" እንደምትሉ አልጠራጠርም። እውነት ነው ቤተክርስቲያን እንደሠራችው ሥርዓት፣ ሐዋርያት እንዳስቀመጡት ቀኖና፣ ሊቃውንት እንዳበጃጁት ቀመር የፍልሰታ ጾም የሚፈታው ነሐሴ 16 የኪዳነ ምሕረት ዕለት ነው። በዚህም ዕለት ነው የዛሬ 1961 ዓመት እመቤታችን ከሞት የተነሣችውና በዚያው ዕለትም ያረገችው።

እኔ ጾመ ፍልሰታ የምትፈታው መቸ ነው? ብየ ስጠይቅ የምትፈታው በሌላ ቀን ሆኖ ያንን ቀን ለመናገር ሳይሆን አሁን አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ያልተማሩና ያልጠነቀቁ ካህናት ካልተማሩና ካልጠነቀቁ ምዕመናን ጋር በመሆን ሐዋርያት ሊቃውንትና መነኮሳት የደነገጉትን ሥርዓት በማፍረስና በማስተሐቀር ጾመ ፍልሰታን እስከ ነሐሴ 21 ቀን እያስጾሙና እየጾሙ የቤተክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት እየጣሱና እያስጣሱ በመታየታቸው የዚህ ግብራቸውን ስሕተትነት ለመግለጥ ነው ጥያቄውን ማንሣቴ።

እርግጥ ነው እኛ ክርስቲያኖች ተድላ ደስታችን በሰማይ ከአምላካችን ዘንድ ነው እንጅ ልበ አምላክ የእግዚአብሔር ነቢይ ቅዱስ ዳዊት ብዑላነ ምድር (የምድር ባለጸጎች) መዝ. 45፥12 ሲል እንደጠራቸውና ተድላ ደስታቸው በዚህች በኃላፊ ጠፊዋ በጊዜያዊዋ ምድር እንደሚፈጸምባቸው በዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማይ ግን ምንም ዕድል ፈንታ ዕጣ ተርታ እንደሌላቸው እንደ አሕዛብ አረማውያን ተድላ ደስታችን በምድር አይደለምና ለጾምና ለትሩፋት

ማድላት ይጠበቅብናልና ለጾም መደላቱ የሚበረታታ እንጅ የሚነቀፍ፣ የሚከፋ ባልሆነ ነበረ፡፡ ሊጣስ ሊገሠሥ የማይገባ ሥርዓትና ቀኖና መጣስ መገሠሡ ነው እንጅ ከፋቱ፡፡

እነኝህ ፍልሰታን እስከ ነሐሴ 21 እየጾሙና እያስጾሙ ያሉ ጨዋ ካህናትና ምዕመናን "ሦስት ሱባኤ ለመሙላት!" ከሚለው ጨዋ ምክንያታቸው በስተቀር ፍልሰታን እስከ ነሐሴ 21 ድረስ ለመጾም ለማስጾማቸው ከመጽሐፍ የሚጠቅሱት ሌላ አንድም ነገር የላቸውም፡፡ ይህ ድርጊታቸውም ከቤተክርስቲያን ሥርዓትና ቀኖና ጋር ምን ያህል ይቃረን አይቃረንም ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ይመስለኛል እንዲህ እንዲያስቡ ያደረጋቸው አባቶች በገዳም የፍልሰታን ጾም ሱባኤ ከዘጉ በኋላ ሱባኤዋን በ14 ማታ ፈጽመው ሰንበትን ካልነካ 15ን አክፍለው በ16 ጾም በመፍታት የእመቤታችንን ትንሣኤና እርገት በዓል አክብረው ከበዓታቸው የሚወጡት ግን በ21 ነው፡፡ ይሄንን የሚያደርጉት እመቤታችን ተነሥታ ካረገችበት ቀን ከ16 እስከ 21 ያሉት ቀናት የእመቤታችን የበዓል ቀናት በመሆናቸውና ሥራ ስለማይሠሩባቸው፣ መንገድ ስለማይወጡባቸው በዓሉን በተገቢው መንገድ ለማክበር ብለው ከበዓታቸው ሳይወጡ መቆየታቸው እንዲህ ማድረጋቸውን የሚያዩ ሰዎች አባቶች ፍልሰታን እስከ 21 የሚጾሙ መስለው እንዲታዩዋቸው አድርጓል፡፡

አባቶች ግን ከ16 እስከ 21 ሳይወጡ የሚቆዩት በዓሏን ለማክበር ነው እንጅ እየጾሙ አይደለም፡፡ ጨዋዎቹ ግን አባቶች እስከ 21 እየጾሙ እየመሰሏቸው "እኛም እንጹም!" ብለው ይጾሙና ያስጾሙ ያዙ፡፡ በመሠረቱ የጨዋዎቹ ሐሳባቸው ሦስት ሱባኤ መሙላት ከሆነ ሊገድፉ ወይም ጾም ሊፈቱ የሚገባቸውና ሦስቱ ሱባኤ የሚጠናቀቀው በ22 ነው እንጅ በ21 አልነበረም፡፡ 21 እማ የሦስተኛው ሱባኤ የመጨረሻ የጾም ቀን ነው እንጅ የሦስተኛው ሱባኤ መጠናቀቂያ ወይም የሦስት ሱባኤ ጾም መፍቻ ቀን አይደለም፡፡ የሦስት ሱባኤ ጾም የሚፈታው በ22ኛው ቀን ነው፡፡ እናም ነገሩ ተጀምሮ እስኪፈጸም የጨዋ ሥራ ነውና እንዲህ ዓይነት ችግር ሊገጥም ቻለ፡፡

ለመሆኑ የፍልሰታን ጾም ወይም ሱባኤ እስከ ነሐሴ 21 ድረስ መጾምና ማስጾም ችግሩ ምንድን ነው? ከየትኛውስ ቀኖናና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ጋር ነው የሚጋጭ የሚቃረነው? ቢባል፦

1ኛ. ሁላችንም እንደምናውቀው ቅዱሳት መጻሕፍትም የደነገጉት የጾሟ ወይም የሱባኤዋ መፈቻ በ16 ነው፡፡ ጾሙን የጀመሩት የሐዋርያት ሁለት ጊዜ ሁሉ በተለያየ ምክንያት አከታትለው ሲጾሙ ሐሳባቸው የነበረው ሱባኤ ለያዙበት ጥያቄ ከጌታ መልስ እስኪያገኙ ድረስ ለመጾም ቆርጠው ሱባኤያቸውን ያዙ እንጅ ለመጀመሪያው ጥያቄያቸው ማለትም ወላዲተ አምላክ በ64 ዘመኗ አርፋ ሐዋርያት ቀብር ሊፈጽሙ ሲሔዱ አይሁድ "ቀድሞ ልጇ ሞትኩ ተነሣሁ አረግሁ እያለ ሲያውከን ኖረ አሁን ደግሞ እሷ ሞትኩ ተነሣሁ አረግሁ እያለች ልታውከንም አይደል! እንነሣና አስከሬኗን እናቃጥለው!" ብለው በሚነሡበት ወቅት መላእክት የእመቤታችንን አካልና ሐዋርያው ዮሐንስን ወስደው በገነት ከዕፀ ሕይዎት ዛፍ ስር አስቀመጧቸው፡፡ ቀበርዋ ይለዋል፡፡

ዮሐንስ ተመልሶ መጥቶ ለሐዋርያት የእመቤታችን አካል በገነት ከዕፀሕይዎት ዛፍ ስር እንደተቀመጠ ሲነግራቸው "ዮሐንስ ያየውን ለማየት!" በሚል ሳነሡት ጥያቄያቸው መልስ ለማግኘት ሽተው ሱባኤ ሲይዙና ሁለተኛውን ሱባኤ አጠናቀው ሦስተኛ ሱባኤ ለመጀመር በሚያስቡበት ጊዜ ለጥያቄያቸው መልስ ሲያገኙ፡፡ በኋላም በዓመቱ እንደገና ሁለተኛ ጥያቄ ይዘው ማለትም በመጀመሪያው ሱባኤያቸው ጥያቄያቸው መልስ አግኝቶ የእመቤታችን አካል ተሰጥቷቸው ወስደው ከቀበሯት በኋላ እሑድ ሥርዓተ ቀብሯን ፈጽመው ማክሰኞ በ16 ተነሥታ ስታርግ በሀገረ ስብከቱ ሕንድ ለሐዋርያዊ ተልእኮ ሲፋጠን እረፍቷንም ቀብሯንም ያልሰማው ቶማስ ደመና ጠቅሶ ሲመለስ እመቤታችንን ስታርግ ቢያገኛት "ቀድሞ ጌታ ልጅሽ ከትንሣኤው ለየኝ አሁን ደግሞ አንቺ ለየሽኝ!" ብሎ ተበሳጭቶ ከደመና ለመውደቅ ሲፈልግ እመቤታችን ሐዋርያት ትንሣኤዋንና እርገቷን እንዳላዩ ነግራው ለወንድሞቹ ለሐዋርያት ምልክት እንዲሆነው የተገነዘችበትን ሰበን ሰጥታው "ተነሣች አረገች!" ብሎ እንዲነግራቸው ላከችው፡፡

ቶማስ ሐዋርያትን እንዳገኛቸው እመቤታችን እንዴት እንደሆነች ይጠይቃቸዋል፡፡ ሐዋርያትም ጥር 21 አርፋ ነሐሴ 14 እንደቀበሯት ይነግሩታል፡፡ ቶማስም "ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር! ይሄስ የማይሆን ነገር ነው!" ብሎ መለሰላቸው፡፡

ሐዋርያው ጴጥሮስም ተቆጥቶ "ቶማስ አንተ መጠራጠር ልማድህ ነው! ቀድሞ የጌታን ትንሣኤ ኣላምንም ብለህ እጅህን በተወጋ ጎኑ ከተህ አቃጠልካት፡፡ አሁን ደግሞ የእናቱን እረፍትና ቀብር አላምን አልክ፡፡ አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም ሕዝቡንም ስታጠራጥር ትኖራለህ እንጅ!" ብሎ አስከሬኗን ሊያሳየው መቆፈሪያውን ይዞ ሔደ፡፡ ቢቆፍር የእመቤታችንን አካል አጣውና ደነገጠ፡፡ ያን ጊዜ ቶማስ "አታምኑኝም ብየ ነው እንጅ እመቤታችንስ ተነሣች አረገች!" ብሎ የገነዙባትን ሰበን አውጥቶ አሳያቸው፡፡ ሐዋርያትም አመኑትና "ቶማስ ትንሣኤሽን እርገትሽን አይቶ እኛ ሳናይ!" ብለው ሱባኤ ሲገቡ ለ 14 ለ 14 ቀን ለመጾም አስበው አልነበረም ሱባኤ የገቡት፡፡ ከጌታ መልስ እስኪያገኙ፣ የልባቸው መሻት እስኪፈጸምላቸው ድረስ ለመጾም አስበው ገቡ እንጅ፡፡

ነገር ግን ተጠያቂው፣ ተለማኙ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሐዋርያት ለያዙት ሱባኤ የመጀመሪያውን በ 14 ኛው ቀን የእመቤታችንን አካል ከነበረበት መልአኩ ከገነት ከዕፀ ሕይዎት ዛፍ ስር አፍልሶ ለሐዋርያት በመስጠት (ጾሚ ወይም ሱባኤዋ ፍልሰታ የተባለውም በዚሁ ምክንያት ማለትም የእመቤታችን አካል ከገነት ወደ ምድር በመፍለሱ ምክንያት ነው) የሁለተኛውን በ 16 ኛው ቀን ጌታ እናቱን አምጥቶ እሷን መንበር፣ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን፣ ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስን ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ ካቆረባቸው በኋላ ትንሣኤዋንና እርገቷን በማሳየት መልሳቸውን ሰጣቸው፣ የልባቸውን መሻት ፈጸመላቸው፡፡

ይሄም ማለት የፍለሰታን ጾም በሁለት ሱባኤ የገደበው እራሱ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ነው እንጅ ሐዋርያት አይደሉም ማለት ነው፡፡ አሁን እንግዲህ ጨዋዎቹ "የፍልሰታን ጾም ወይም ሱባኤ እስከ 21 ቀን ድረስ እናደርሳለን ወይም ሦስት ሱባኤ እንጾማለን!" ሲሉ የፍልሰታን ጾም ወይም ሱባኤ በሁለት ሱባኤ የገደበውን ወይም የወሰነውን መድኃኔዓለም ክርስቶስን እያስተሐቀሩ "ትክክል አይደለህም ሱባኤው ሦስት ነው መሆን ያለበት!" ማለታቸው እንደሆነ ሊረዱ አልቻሉም፡፡ ሰዎቹ ጾም የመጾም፣ ሱባኤ የመያዝ ፍቅር ካገበራቸው፣ ትሩፋት ማብዛት ከፈለጉ በሌላ ጊዜ በዓሉን አሳልፈው ይሄንን ፍቅራቸውንና ፍላጎታቸውን እስከፈለጉት ቀን ድረስ በመጾም ሊወጡ ይችላሉ እንጅ ባልገባቸው ነገር ላይ ወስነው ሥርዓትና ቀኖናን በመጣስ ሊጾሙና ሊያስጾሙ አይችሉም፡፡

2 ኛ. ይሄንን የእመቤታችንን የትንሣኤና የእርገት በዓል (ነሐሴ 16 ን) እንደልጇ ትንሣኤና እርገት በዓል አድርገን በፍጹም ደስታና ሐሴት እንድናከብር ሊቃውንቱና እንደነ አባ ሚካኤል አባ ገብርኤል ያሉ ዐበይት መነኮሳት አዘዋል የግዝት ቃልም አስፍረዋል፡፡ እራሷ ወላዲተ አምላክም ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ እንደተቀመጠው በሁለተኛው ሱባኤ ልጇ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ነሐሴ 16 ቀን የእናቱን ትንሣኤና እርገት ባሳያቸው ቀን "ትንሣኤየን እንደልጀ ትንሣኤ አድርጋቹህ አክብሩት!" ብላ ለሐዋርያቱ ተናግራለች፡፡ በዚህም መሠረት ቤተክርስቲያን ከ 16 እስከ 21 ያሉ ቀናትን ልክ እንደ በዓለ ሐምሳ ሁሉ በዓል አድርጋ ቅዳሴው የበዓል ቅዳሴ ዕዝል ነው፡፡ እስከ 21 የሚሰበከው ምስባክም የእመቤታችን ምስባክ ነው፡፡ ሌላው ቀለም ሁሉ የበዓል ቀለም ነው፡፡ እዚህ ላይ መናገር የምፈልገው ነገር ቢኖር ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ቀኖናና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ከሐዋርያት የቀረውን ሊቃውንቱ እንዳሟሉት ከቀደምት ሊቃውንት የቀረውን ደኃርት ሊቃውንት ያሟሉት ዘንድ ኃላፊነትና ግዴታም አለባቸውና ወላዲተ አምላክ "ትንሣኤየን እንደ ልጀ ትንሣኤ አድርጋቹህ አክብሩት!" ብላ እያለች የእመቤታችን ትንሣኤ በዓል ቀን እንደ የጌታ ትንሣኤ በዓል ቀን እሑድን የማይለቅ ባለመሆኑና እንደ የጌታ የልደት በዓል ቀን ተቀያያሪ በመሆኑ የእመቤታችን የትንሣኤ በዓል ቀን ረብዑ እና ዐርብ ሲውል እንደ የጌታ ልደት በዓል የብሎት ወይም የፍስክ ቀን መሆን ነበረበት እንጅ የጾም ቀን መሆን አልነበረበትምና ይሄንን ነገር የማሟላቱ ድርሻ በዘመናችን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ትከሻ ላይ ወድቋልና ሊቃውንቱ ይሄንን ነገር ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ የወላዲተ አምላክ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ቃል ነውና፡፡

እናም እንግዲህ ከላይ የተገለጹት ነገሮች እያሉ በፍጹም ደስታና ሐሴት በታላቅ ክብር ማክበር የሚገባንን የእመቤታችንን የትንሣኤና የእርገት በዓል በሱባኤ ወይም በሐዘን ካሳለፍን ከላይ እንደጠቀስኩት በግዝት ታስረናል ማለት ነው፡፡ ስሕተቱም ቀኖና የሚያስፈልገው ጥፋት ነው፡፡ የእመቤታችንን በዓል መጻሕፍት እንደደነገጉት፣ አበው ሊቃውንት እንዳዘዙት በቀኑ ሳናከብር በጾም በሱባኤ ማለትም በሐዘን የምናሳልፍበት የሚጠቀሰው ምክንያት ቀና መሰለ እንጅ ይህች ሥራ በወላዲተ አምላክ ክብርና ልዕልና የሚቀናው የሚቃጠለው ለማስተሐቀርም ሌት ተቀን የሚጥረው የሰይጣን የተንኮል ሥራ ናት፡፡

ነሐሴ 21 ቀን ወርሐዊ በዓል ነው እንጅ ዓመታዊ በዓል አይደለም፡፡ በመሆኑም እንደታዘዝነው ሁሉ እስከዛሬ ድረስ ይሄንን በፍጹም ደስታና ሐሴት በታላቅ ክብር ማክበር የሚገባንን የእመቤታችንን የአምላክ እናትን ዐቢይ በዓል በመሻር በጾም ወይም በሱባኤ (በሐዘንና ለቅሶ) ያሳለፍን ሰዎች በግዝት ታስረናልና የታሰርንበትን ግዝት እናስፈታና ለከእንግዲሁም እንታረም እንጠነቀቅ ዘንድ የአባቶችን የአደራ ቃል አስተላልፋለሁ፡፡

ፍልሰታን ለምን እንጾማታለን?፡-

እኛ ክርስቲያኖች ፍልሰታን ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ጾም የምንጾምበት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ስፍራዎች እንደተገለጸው
1 ኛ. መንፈሳዊ ኃይል ከእግዚአብሔር ለማግኘት ለምሳሌ እንደ ነቢዩ ዳንኤል ትን. ዳን. 10፥1-21
2 ኛ. ከአምላክ ጋር ለመገናኘት ለምሳሌ እንደ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ዘጸ. 34፥28
3 ኛ. ረድኤተ እግዚአብሔርን ለማግኘት ወይም እግዚአብሔር እንዲያደርግልን የምንፈልገው ነገር ሲኖር ለምሳሌ እንደ አስቴር መጽ. አስ. 4፥1-17
4 ኛ. በመተላለፋችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ከሚመጣብን ቁጣ፣ መቅሰፍት፣ ቅጣት ለመዳን ለምሳሌ እንደ ነነዌ ሰዎች ትን. ዮና. ም. 1-4
5 ኛ. ሰው እንደመሆናችን መጠን ሰውነታችን ሲመቸው፣ ሲደላው፣ ሲወፍር፣ ሲዳብር ኃጢአትን ስለሚጋብዝ፣ ለኃጢአት ሥራዎች ስለሚሸነፍ ስለሚንበረከክ፣ ሥጋዊ አስተሳሰብና የዐመፃ ተግባር ስለሚሠለጥንበት፣ መንፈሳዊ አስተሳሰብና ተግባራት ስለሚርቁት እንዲህ እንዲህ ዓይነት ችግሮች እንዳይገጥመን፣ ሥጋችንን ሰውነታችንን ለመገሰጽ፣ ለመለጎም፣ ለመቀየድ ባጠቃላይ እራሳችንን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ጾምን ከምንጾምበት በተጨማሪ ፍልሰታን የምንጾምበት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል የጻድቃን ወይም የቅዱሳት መታሰቢያ ለበረከት ነው ይላልና መዝ. 10፥7 እመቤታችንን በጾም በዝክር ወዘተረፈ. በማሰብ የወላዲተ አምላክን ረድኤት በረከት ለማግኘት ፣ መድኃኔዓለም ክርስቶስ እናቱን በእናትነት የሚሸልማት እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ ዮሐ. 19፥25-27 ለስቃይ ለመከራ ለፈተና ሳይበገሩ እስከ ቀራንዮ ድረስ በጽናት ለተከተሉት፣ ለታመኑለት ነውና መተላለፋችንን ሳያስብ በቸርነቱ "እነኋት እናታቹህ!" ብሎ እናትነቷን ሰጥቶን በእናትነቷ ረድኤትና ጥበቃ ጥላ ስር ያሳርፈን ዘንድ ለመማጸን እኛም የፍልሰታን ሱባኤ ከሐዋርያት ተቀብለን በጾም በጸሎት በሥግደት እናሳልፋለን፡፡ ይቆየን! መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከእናቱ ረድኤት በረከት ይክፈለን! ከእናትነቷ ጥበቃ ጥላ ስር ያሳርፈን አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለ መስቀሉ ክቡር አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com